Australian Government

Inspector-General of Taxation

Taxation Ombudsman

የግብር ቅሬታ?

Amharic

የእኛ ማንነት

አጠቃላይ ተቆጣጣሪ እና ለግብር አቤቱታ ሰሚ (Inspector-General & Taxation Ombudsman (IGTO)) በራሱ የሚተዳደር የፌደራል መንግሥት ድርጅት ሲሆን በአውስትራሊያ ግብር ቢሮ (Australian Taxation Office (ATO)) እና በታክስ ባለሙያዎች ቦርድ (Tax Practitioners Board (TPB)) ስለሚካሄድ የአስተዳደር ድርጊት በተመለከተ እርስዎን ለመርዳት ሃላፊነት አለው።

1300 44 88 29
(በአካባቢ ስልክ ጥሪ ዋጋ)

እንዴት ልንረዳዎ እንደምንችል

የርስዎን ቅሬታ ለማቅረብ ለመርዳት በማንም ተጽእኖ የሌለበት፤ ነጻና የግብር ልዩ ባለሙያ አገልግሎት እናቀርባለን።

'አስተዳደራዊ ድርጊት' ለቦርድ የሥራ ጊዜ ሲሆን በአጠቃላይ ስለ ATO ወይም TPB ተገቢና ምክንያት ያለው ድርድር ከርስዎ ጋር ማካሄድን ያካትታል።

የIGTO ሊረዳዎ እንደሚችል ምሳሌዎች ሲሆን፤ ነገር ግን በነዚህ የተወሰነ አይደለም:

- ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የጊዜ ገደብ;
- የATO ወይም TPB ሀላፊዎች ስነምግባር;
- በመስመር ላይ አገልግሎቶች አቅርቦት;
- በATO ወይም TPB ድርጊት ላይ ዋስትና ያለው ወይም ብቃት ያለው ማብራሪያ;

- የATO ወይም TPB ድርጊቶች ካላቸው ፖሊሲዎችና አሰራር ሂደት ስምምነት መሰረት ስለመሆኑ ማረጋገጥ; እና
- የATO ወይም TPB ከርስዎ ጋር ሲደራደር በአግባቡ እና በመደማመጥ መልኩ እና ሁሉም ጠቃሚ መረጃ እንደቀረበ ግምት ውስጥ ማስገባት፤ ይህም ኦዲት ቁጥጥርና የማጣሪያ ምርመራ ያካተተ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይሆናል።

እኛ መርዳት እንደምንችል እርግጠኛ ካልሆኑ፤ እባክዎ ያነጋግሩን።

እርስዎን በቀጥታ መርዳት ካልቻልን፤ እርስዎን ሊረዳ ወደሚችል ትክክለኛ ድርጅት ወይም አካል እንዲሄዱ የተቻለንን ያህል ምክር እናቀርባለን።

GPO Box 551, Sydney NSW 2001

የቅሬታ ማቅረብ ሂደት

በእኛ ቢሮ ያለዎትን ቅሬታ ለማስገባት፤ “እኛን እንዴት ማነጋገር” (How to contact us) የሚለውን ክፍል ማየት።

ያለዎትን ቅሬታ ካስገቡ በኋላ በ2 የሥራ ቀናት ውስጥ ስለቅሬታዎ መድረስ ለማሳወቅና ከርስዎ ጋር ለመወያየት የ IGTO አጣሪ ሀላፊ ያነጋግርዎታል።

ከተቻለም፤ የርስዎ ቅሬታ በቀጥታ እንዲደርስ እንረዳለን።

የርስዎን ቅሬታ ATO ወይም TPB በተሻለ እንዲረዳና እርስዎን እንዴት በጥሩ መርዳት እንደሚቻል ውሳኔ እንድናካሂድ፤ ከርስዎ የበለጠ ተጨማሪ መረጃ ያስፈልገን ይሆናል።

ያለንን ወቅታዊ እድገት መሻሻል እዲያውቁ እና በሥራ ሂደት ላይ ስለምናካሂደው የማጣራት ጊዜ መጠን ገደብ እናቀርብልዎታለን።

እንዴት እኛን ማነጋገር እንደሚቻል

www.igt.gov.au

1300 44 88 29
(በአካባቢ ስልክ ጥሪ ዋጋ)

GPO Box 551
Sydney NSW 2001

ከእንግሊዝኛ ባሻገር በሌላ ቋንቋ ቅሬታ ማስገባት ከፈለጉ ለትርጉምና አስተርጓሚ አገልግሎት (Translating and Interpreting Service (TIS)) በስልክ **131 450** አድርጎ መደወል።

የመስማት ወይም የመናገር ጉድለት/ችግር ካለብዎት እና ትክክለኛ በሆነ ተለፎን ጽሁፋዊ (TTY) ወይም በዘመናዊ መሳሪያ ለመጠቀም፤ በስልክ **13 36 77** አድርጎ መደወል።

በተለፎን ጽሁፋዊ (TTY) ወይም በዘመናዊ መሳሪያ መጠቀሚያ ከሌለዎት፤ በስልክ ንግግር ወደ ንግግር ማስተላለፊያ አገልግሎት (Speech to Speech Relay Service) በስልክ **1300 555 727** አድርጎ መደወል።